# የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

# የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ

ሰኔ 2006

# መግቢያ

እያደገ ከመጣው የጤና ተቋም አገልግሎት ጋር በተያያዘ የማስተዋወቅ ተግባር በማናቸውም መንገድ የሚተላለፍበት ሁኔታ ደረጃውን ባልጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሁም ሙያዊ ስነ ምግባርን ባላከበረ ማስተዋወቅ ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የጤና ችግር መግታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ ከመተላለፉ ወይም በሌላ የማስተዋወቂያ ማስተላለፊያ መንገድ ከመተዋወቁ አስቀድሞ ዘርፉ የሚመራበትን ህግና ስርዓት መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ በሚተዋወቅበት ጊዜ የህክምና ስነ-ምግባር፣ የህብረተሰቡን ባህል፣ እውቀት እና ልምድ ከግንዛቤ ያስገባ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጤና ተቋም አገልግሎት አሰጣጥ ማስተዋወቅ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲመራ ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 50(1) እና 55 (3) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ ቁጥር 25 /2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2.ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "የጤና ተቋም ማስታወቂያ" ማለት የጤና ተቋም አገልግሎት፣ ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት፣ መረጃ ወይም ሌላ ተዛማጅ መልዕክት እንዲተዋወቅ በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፍ የንግድ ማስታወቂያ ነው፤

2) "የማስታወቂያ አስነጋሪ" ማለት በማስታወቂያ ማስተላለፊያ መንገድ አማካኝነት አገልግሎቱ፣ ስሙ፣ አርማው፣ ምልክቱ፣ አላማው ወይም ሌላ ተመሳሳይ መልዕክት የሚነገርለት ወይም የሚተዋወቅለት ሰው ነው፤

3) "የማስተዋወቂያ ማስተላለፊያ መንገድ" ማለት ማስታወቂያ ለማስተላለፍ የሚያገለግል የመገናኛ ብዙኃንን፣ የውጭ ማስታወቂያን፣ ዐውደ-ርዕይን፣ ትምህርታዊ ዝግጅትን፣ ቴሌኮሙኒኬሽንን፣ የፖስታን፣ የኢንተርኔት ድረ ገፅን የፋክስ አገልግሎትን፣ ሲኒማን፣ ፊልምን፣ ቪዲዮን፣ ኔትዎርኪንግን ሲሆን መሰል የማስተዋወቂያ መንገድንም ይጨምራል፤

4) "አግባብ ያለዉ አካል" የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ተግባራትን በክልል ደረጃ የማከናወን ስልጣን የተሰጠው የክልል መንግስት አካል ነው፤

5) "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

6) "የማስታወቂያ አስተላላፊ" ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የአየር ጊዜ፣ የሕትመት ሽፋን ወይም መሰል አገልግሎት በመስጠት ማስታወቂያ የሚያስተላልፍ ሰው ነው፤

7) "የማስታወቂያ አስነጋሪ" ማለት በማስታወቂያ ማስተላለፊያ መንገድ አማካኝነት ማስታወቂያ የሚተዋወቅለት የጤና ተቋም ነው፤

8) "መገናኛ ብዙሃን" ማለት የሕትመት መገናኛ ብዙሃን እና የብሮድካስት አገልግሎትን ያካትታል፤

9) "የብሮድካስት አገልግሎት" ማለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ነው፤

10) "ተካታች ማስታወቂያ" ማለት ብሮድካስተሩ ገንዘብ የተቀበለበትን ወይም ጥቅም ያገኘበትን የማንኛውንም የጤና ተቋም አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት በፅሁፍ ወይም በድምጽ ወይም በምስል በተዘዋዋሪ ለማስተዋወቅ ከአንድ ፕሮግራም ጋር የተካተተ ማስታወቂያ ነው፤

11) "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት አግባብ ካለው አካል ለጤና ተቋም የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው፤

12) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

13) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3.የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4.የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፡-

1) የጤና ተቋም አገልግሎትን በንግድ ማስታወቂያ የሚተላለፍበትን ሁኔታ ለመወሰን፤

2) የማስታወቂያ መልእክቶች በተጋነነና ተገቢ ባልሆነ መልኩ በማስተላለፍ በህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትሉትን የስነ ልቦና ጫና ለመከላከል፤

3) የሚተላለፉ የማስታወቂያ መልእክት የህክምና ስነ ምግባርን በጠበቀ መልኩ እንዲሆን ለማድረግ፤

4) ማስታወቂያ የሚነገርላቸው የጤና ተቋማት የሚሠጡትን የጤና አገልግሎት መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥና በተሳሳተ መረጃ ሊደርስ ከሚችል ጉዳት ህብረተሰቡን ለመጠበቅ፡፡

# ክፍል ሁለት

## የጤና ተቋም አገልግሎት ማስተዋወቅ

### 5.መርህ

ማንኛውም ማስታወቂያ አስነጋሪ በመገናኛ ብዙሀን አማካኝነት የጤና ተቋሙን አገልግሎት ለማስተዋወቅ ባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው አካል የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

### 6.ስለ ማስተዋወቅ

ማንኛውም ማስታወቂያ አስነጋሪ፦

1) የሚሰጠውን አገልግሎት በሚያስተዋውቅበት ጊዜ ማስታወቂያውን በአማርኛ ወይም በአካባቢው ቋንቋ የተዘጋጀ ሆኖ ህብረተሰቡ ሊረዳው በሚችል አገላለጽ መሆን አለበት፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ማስታወቂያው በሚገለጽበት ጊዜ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፦

(ሀ) የሚተዋወቀውን የጤና ተቋም ሙሉ ስም፣

(ለ) የሚተዋወቀው ጤና ተቋም አገልግሎቱን የሚሰጥበት አድራሻ፣

(ሐ) ጤና ተቋሙ የሚሰጠውን አገልግሎት፤

(መ) ጤና ተቋሙ አገልግሎቱን የሚሰጥበት ሰዓት፣ እና

(ሠ) የጤና ተቋሙን ደረጃ፣

3) አገልግሎቱን በሚያስተዋውቅበት ጊዜ የሌሎች ጤና ተቋማትን የሚሰጡትን አገልግሎትና የጤና ባለሙያዎችን ሙያ ዝቅ የሚያደርግ እና የሚያንቋሽሽ መሆን የለበትም፤

4) በጤና ተቋሙ ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ከሌሎች ባለሙያዎች የተሻሉ የሙያ ብቃትና እውቀት ያላቸው በማስመሰል የሚገልፅ መሆን የለበትም፤

5) ጤና ተቋሙ ስለሚሰጠው አገልግሎት ሲያስተዋውቅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አላስፈላጊ የሆነ የተገልጋይን ተነሳሽነት ሊፈጥር በሚችል ሁኔታ ማለትም እንደ ስጦታ፣ የዋጋ ቅናሽ፣ ማበረታቻ፣ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም የሚያስገኝ አድርጐ መግለጽ የለበትም፤

6) በጤና ተቋሙ አገልግሎት ያገኘ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ጤና ተቋሙ ስለሚሰጠው አገልግሎት ምስክርነት እንዲሰጥ ማድረግ የለበትም፤

7) በማስታወቂያው ላይ የጤና ተቋሙን አገልግሎት ካላገኙ በጤናቸው ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ የሚያሳይ ሆኖ መገለጽ የለበትም፤

8) ጤና ተቋሙ ስለሚሰጠው የጤና አገልገሎት ጥራት ወይም የህክምና ምርምሮች እና ውጤቶች በተመለከተ አገራዊ ወይም አለማቀፍዊ ሽልማት ያገኘ ከሆነ ስላገኘው ሽልማት ወይም እውቅና ሲያስተዋውቅ ሽልማቱ ወይም እውቅናው የተሰጠበትን ወቅት እና ምክንያት በመጥቀስ ትክክለኛውን መረጃ ማስተዋወቅ ይኖርበታል፤

9) ጤና ተቋሙ አገልግሎት ለመስጠት ልዩ የሆነ ንጥረ ነገር እንደሚጠቀም ወይም የተለየ ፈውስ የሚገኝበት ተቋም እንደሆነ በማስመሰል ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ የለበትም::

## 7. በስፖንሰር ስለሚቀርብ ማስታወቂያ

ማንኛውም በስፖንሰር የሚቀርብ የጤና ተቋም ማስታወቂያ ይዘት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆን አለበት፡፡

## 8. ስለተካታች ማስታወቂያ

ማንኛውም የጤና ተቋም ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያያዥነት የሚኖረውን ነገር በብሮድካስተር ከአንድ ፕሮግራም ጋር አካቶ በፅሁፍ፣ በምልክት፣ በምስል፣ በድምፅ ወይም በሌላ መንገድ ሲያስተዋውቅ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆን አለበት፡፡

# ክፍል ሦስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 9. ማስታወቂያ አስነጋሪው ሃላፊነትና ግዴታ

ማንኛውም ማስታወቂያ አስነጋሪው የሚያዘጋጀው ወይም እንዲዘጋጅለት የሚያደርገው የጤና ተቋሙ ማስታወቂያ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 10.የማስታወቂያ አስተላላፊ ሃላፊነትና ግዴታ

ማንኛውም ማስታወቂያ አስተላላፊ እንዲያስተላልፍ የሚቀርብለትን የጤና ተቋም ማስታወቅያ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤

## 11.መረጃ ይዞ ስለማቆየት

ማንኛውም የማስታወቂያ አስተላላፊ የሚያሰተላልፋቸውን የጤና ተቋማት ማስታወቂያ ቢያንስ ለስድስት ወር ይዞ ማቆየት ይኖርበታል፤

## 12.ስለአፀፋ ማስታወቂያ

ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ ወይም አስተላላፊ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማስታወቂያ ሲያስነግር ወይም ሲያስተላልፍ እንደ አስፈላጊነቱ ጉዳት

የደረሰበት ሰው አፀፋ ማስታወቂያ እዲተላለፍ ለኢትዮጲያ ብሮድካስት ባለስልጣን ጥቆማ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 13.የመተባበር ግዴታ

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 14.ቅጣት

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ተላልፎ ሲገኝ ዘርፉ የሚመራበት ስለምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የወጣ አዋጅ ቁጥር 661/2002 እና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች መሰረት በሕግ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 15.ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 16.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ቀን ከ ሀምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**የሁሉ ደነቀው**

**የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

## ማውጫ

ገጽ

መግቢያ…………………………………………………………………………...1

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ…………………………………………………………………………2
2. ትርጓሜ……………………………………………………………………………..2
3. የተፈፃሚነት ወሰን………………………………………………………………….3
4. የዚህ መመሪያ አላማዎች…………………………………………………………..3

## ክፍል ሁለት
## የጤና ተቋም አገልግሎት ማስተዋወቅ

5. መርህ……………………………………………………………………………...4
6. ስለ ማስተዋወቅ………………………………………………………………...……4
7. በስፖንሰር ስለሚቀርብ ማስተዋወቅ……………………………………………….....6
8. ስለ ተካታች ማስታወቂያ…………………………………………………………….6

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. የማስታወቂያ አስነጋሪው ሃላፊነትና ግዴታ ………………………………………………6
10.የማስታወቂያ አስተላላፊ ሃላፊነትና ግዴታ ……………………………………………..6
11መረጃ ይዞ ስለማቆየት……………………………………………………………….6
12. ስለ አጸፋ ማስታወቂያ………. ………………………………………………………6
13. የመተባበር ግዴታ………………………………………………………………….7
14. ቅጣት…………………………………………………………………………….7
15. ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች……………………………………………………....7
16. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ………………………………………………………....7